1453

መውሊድ

በቁርኣን ፣ በሀዲስ እና በሰለፎች እይታ





https://t.me/sufiyahlesuna

መውሊድ በቁርኣን ፣ በሀዲስ እና በሰለፎች እይታ

መንደርደሪያ

ዓለም በብርሃን ድርቅ ተመታለች፤ ጽልመቱ በማን አለብኝነት ስሜት ይንጎማለላል። ሥነ-ምግባር ጃጅቶ ሊሞት ያጣጥራል፤ ፍትሕ ሸሽቶ በደል ነግሷል። እዝነት በጭካኔ ተተክቷል፤ አቅመ ደካማው ሕይወት እሬት እሬት ብሎታል። ሴት በሕይወት የመኖር መብቷን "የእኔ" በምትላቸው አካላት ተነጥቃለች። ሕገ-ልቦና ጥልቅ ተቆፍሮ ተቀብሯል፤ በጥቅሉ ዓለም በድርብርብ ጽልመት ውስጥ ተዘፍቃለች።

በዚህ አስጨናቂ ጊዜ ነበር የአለሙ ብርሃን በጌታቸው ፈቃድ ዓለሙን ከድቅድቁ ጨለማ ሊያወጡት ጽልመቱን ገፈው የዘለቁት። እርሳቸው በመጡ ጊዜ ሴት ልጁን በሕይወት የሚቀብረው ማኅበረሰብ ለእንስሳት መጨነቅ ጀመረ፤ በደል ተገፎ ፍትሕ ሰፈነ፤ ከጠባብነት ወደ ሰፊነት የሰው ልጅ ተሻገረ። ሥነ-ምግባር በእንክብካቤ እንደተያዘ ቡቃያ ያለ ልክ አበበ፤ እምነት በሰዎች ልብ ስር እንደ ጅረት ፈሰሰ።

የዚህ ሁሉ ጸጋ ሰበብ ደግሞ የፍጡራን አይነታ፣ የከውኑ ሞገስ፣ የዓለሙ ብርሃንና የሰው ልጆች የነፃነት አውጪ የሆኑት የአላህ መልክተኛ ሙሐመድ ኢብኑ ዐብደላህ (ﷺ) ናቸው።

ኢማሙ ሻፊዒ ተብለው የሚታወቁት ታላቁ የኢስላም ሊቅ (150-203 ሂጅሪያ) የኖሩት «አር-ሪሳላህ» በተባለው መጽሐፋቸው እንዲህ ይላሉ፦

يَقُولُ الإِمَامُ الشَّافِعِيُّ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ وَأَرْضَاهُ: "أَصْبَحْنَا وَمَا مِنْ نِعْمَةٍ ظَاهِرَةٍ أَوْ بَاطِنَةٍ إِلَّا وَسَبَبُهَا سَيِّدُنَا رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ

> "ማንኛውም ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ የተለገስነው ጸጋ ሁሉ ሰበቡ ሰይዲና ሙሀመድ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ናቸው።"

የጸጋው ታላቅነት

አላህ (ሱ.ወ) ራሱ ለሙእሚኖች ትልቅ ጸጋ እንደዋለላቸው በቁርኣኑ እንዲህ ሲል ይገልጻል፦

{لَقَدْ مَنَّ اللَّهُ عَلَى الْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ} [آل عمران: ١٦٤]

"አላህ በምእመናን ላይ ከራሳቸው የኾነን መልክተኛ በውስጣቸው በላከ ጊዜ በእርግጥ ታላቅ ችሮታ ለገሳቸው።"

ሸይኽ ኢብኑ ተይሚያ (ረሒመሁላህ) ይህንን መለኮታዊ ጸጋ ሲገልጹ እንዲህ ይላሉ፦

قَالَ الإِمَامُ ابْنُ تَيْمِيَّةَ -رَحِمَهُ اللَّهُ-: "وَمَنِ اسْتَقْرَأَ أَحْوَالَ الْعَالَمِ تَبَيَّنَ لَهُ أَنَّ اللَّهَ لَمْ يُنْعِمْ عَلَى أَهْلِ الْأَرْضِ نِعْمَةً أَعْظَمَ مِنْ إِنْعَامِهِ بِإِرْسَالِهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ

"የዓለምን ሁኔታ በጥልቀት ያጠና ሰው፣ አላህ ለምድር ነዋሪዎች ነብዩን (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ከመላክ የበለጠ ታላቅ ጸጋ እንዳልለገሳቸው በግልጽ ይረዳል።"

ነብዩም (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ራሳቸውን ሲገልጹ እንዲህ ብለዋል፦

((أَيُّهَا النَّاسُ، إِنَّمَا أَنَا رَحْمَةٌ مُهْدَاةٌ))

"እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ (ለዓለም) የተሰጠሁ እዝነት (ራሕመት) ነኝ።"

የሰሐቦችና የሰለፎች ታላቅ ፍቅር

በተለይ በጥልቀት የተረዷቸው ውድ ባልደረቦቻቸው (ሰሐቦች) በፍቅራቸው ዋለሉ። ሁሉም ባልደረባ የራሱ በሆነ መንገድ ፍቅሩን ይገልፅ ነበር። ለምሳሌ፦
ሰይዲና ዐምር ኢብኑል ዓስ፦ ከግርማ ሞገሳቸውና ከፍቅራቸው የተነሳ ቀና ብሎ ማየት የማይችል፣ "እስኪ ምን ይመስሉ ነበር?" ተብሎ ቢጠየቅ መግለጽ የማይችል ነበር።

ሰይዲና ሐምነህ ቢንቱ ጆሕሽ፦ በኡሑድ ጦርነት አባቷን፣ ወንድሟንና ባሏን ማጣቷን እየረዷት፣ ምንም ሳይመስላት የነብዩን ደህንነት ብቻ የምትጠይቅና "እርሶ ደህና ከሆኑማ መከራው ሁሉ ቀላል ነው" በማለት ፍቅሯን የገለጸች ድንቅ ሴት።

ሰይዲና ሰውባን (ረ.ዐ)፦ ከነብዩ (ﷺ) ትንሽ ሲርቅ ፊቱ ገርጥቶ፣ አካሉ ከስቶና ቀለሙ ተቀይሮ የሚጠብቃቸው አፍቃሪ።

ሰይዲና ኹበይብ (ረ.ዐ)፦ በሞት አፋፍ ላይ ሆኖ "እኔ ከቤተሰቤ ጋር በሰላም ተቀምጬ ነብዩ (ﷺ) እሾህ እንኳን እንዲወጋቸው አልፈልግም" ሲል በግልጽ ያወጀ።

ሰይዲና ቢላል (ረ.ዐ)፦ ሞት አፋፍ ላይ ደርሶ "ነገ ከነብዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እና ከወዳጆቻቸው ጋር ልገናኝ ነው!" እያለ በደስታ የፈነጠዘ።

ገሚሱ ደማቸውን ይጠጣል፣ ሌላው ላባቸውን ለሽቶ መስሪያ ይቀዳል፤ ከፊሉ ውዱእ ያደረጉበትን ውሃ ለመውሰድ

ይጋደላል፤ ጸጉራቸውን ለመካፈል ይጣጣራል። ይህ ሁሉ ፍቅራቸውን ማሳያ ነው። ሰሐቦችን የተመለከተ ሁሉ የሚሰጠው ምስክርነት፦ "የሙሐመድ ባልደረቦች ሙሐመድን እንደሚወዱትና እንደሚያከብሩት ማንም በማንም አልተወደደም፣ አልተከበረም" የሚል ነበር።
በኋላ የመጣው ትውልድም (ታቢዒዮችና የሰለፍ ሊቃውንት) ይህንን ፍቅር ወርሰዋል፦

አማሙ ማሊክ፦ ነብዩ ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም በእግራቸው የረገጡትን ምድር በመጓጓዣ አልጓዝም በማለት በእግራቸው ይጓዙ ነበር ፣ ስለ ነብዩ (ﷺ) ሲናገሩ ፊታቸው ይቀያየር ይላዋወጥ ነበር።

ኢብኑ መንከዲር፦ የነብዩን (ﷺ) ስም ሲያነሱ የሚያለቅሱ።

ሳቢቱል ቡናኒ፦ የነብዩን እጅ የነካውን ሁሉ የሚስሙ። አንድ ቀን የነብዩ አገልጋይ የነበሩት አነስ (ረ.ዐ) ለሳቢቱል ቡናኒ ፖም ወረወሩላቸው፤ እርሳቸውም ቀበል አድርገው ፖሙን ሳም አደረጉትና፦ "የአላህን መልክተኛ እጅ የነካ እጅ የነካው ፖም!"አሉ።

የመውሊድ አስፈላጊነትና ወቅታዊ እውነታዎች

ከጊዜ በኋላ ሰዎች ለነብዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ያላቸው ፍቅርና ክብር እየቀነሰ መጣ፤ በተለይም ስለ እርሳቸው ያላቸው እውቀት ማነሱ ችግሩን የበለጠ አስጊ አደረገው። ለዚህም ነው የእርሳቸውን ውልደት (ዊላዳህ) ምክንያት በማድረግ ሰዎች ስለ ነብዩ (ﷺ) ትውውቅ የሚያደርጉት፣ በሳቸው ፍቅር የሚዋለሉትና የተዳፈውን የፍቅር ረመጥ የሚያቀጣጥሉት።

ይህ ተግባር መውሊድ ሲሆን የብዥታ አቦራ ይገሳል እንጂ ሰዎችን ወደ ቁርኣን ለማቅረብና ታዳጊዎች ቁርኣን እንዲቀሩ ለማበረታታት የተለያዩ ፕሮግራሞች (የቁርኣን ውድድር፣ የቁርኣን ምርቃት...) ፕሮግራሞች በየአመቱ ይዘጋጃል ። እነዚህ ፕሮግራሞች በሰለፎች ዘመን በዚህ መልኩ አይታወቁም ምክንያቱም ፣ ሰለፎች ከቁርኣን ጋር የነበራቸው ዝምድና ጠንካራ ስለነበር እንዲህ ዓይነት የማበረታቻ ፕሮግራም አያስፈልጋቸውም ነበር። እኛ ግን ከቁርኣን የራቅን በመሆናችን የዚህ ዓይነት ፕሮግራሞች ጠቀሜታቸው እጅግ የበዛ ነው።

ሌላው ማሳያ ደግሞ፣ ሙስሊሞች የጎዳና ተጠቃሚ መሆናቸውንና የጋራ ሀብትን ለማስጠበቅ ተብሎ በየዓመቱ በረመዳን ወር የሚዘጋጀው "የጎዳና ኢፍጣር" ነው። ይህ ከመውሊድ የሚለየው በቡድንተኝነት አስተሳሰብ ብቻ እንጂ ይዘቱ አንድ ነው።

በመሆኑም መውሊድ ከሸሪዓ ጋር የማይፃረር ተግባር መሆኑን ከቁርኣን፣ ከሐዲስና ከሰለፎች ንግግር በመጥቀስ ሕዝቡን ወደ አንድነት ለማምጣት ታስቦ የተዘጋጀ በራሪ ወረቀት ነው። አላህ ሁሉንም ወደ ቅኑ መንገድ ይመራው ዘንድ ዱዓችን ነው።

የመውሊድ ሥራዎች በቁርኣንና በሐዲስ ሲቃኙ

1. በነብዩ (ﷺ) መደሰትን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ ይላል፦

قُلْ بِفَضْلِ اللَّهِ وَبِرَحْمَتِهِ فَبِذَٰلِكَ فَلْيَفْرَحُوا هُوَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ [يونس: ٥٨]
ትርጉም፦ "በአላህ ችሮታና በእዝነቱ (ምክንያት)፤ በዚህም ይደሰቱ፤ እርሱ ከሚሰበስቡት (ሀብት) ሁሉ የተሻለ ነው በላቸው።" (ዩኑስ: 58)
ታላቁ የቁርኣን ሊቅና የነብዩ (ﷺ) የአጎት ልጅ የሆኑት ዐብዱላህ ኢብኑ ዐባስ (ረ.ዐ) "ራሕመት" የሚለውን ቃል ሲተረጉሙ፦ «ራሕመት የተባሉት ነብዩ (ﷺ) ናቸው» ብለዋል። ኢማሙ ሲዩጢ «አድ-ዱሩል መንሱር» በተባለው ተፍሲራቸው ላይ ይህንን ዘገባ ጠቅሰውታል።

ዕዉቁን የተፍሲር ሊቅ ሸኽ አልአሉሲ አንቀፁን ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል፦

والمشهور وصف النبي صلى االله عليه وسلم بالرحمة كما يرشد إليه قوله تعالى : { وما أرسلناك إلا رحمة للعالمين [الأنبياء : 107]
‹‹ነብዩ እዝነት መባላቸዉና መሆናቸዉ የታወቀ ነው። አላህ እንዲህ በማለት ገልጹዋቸዋልና፦

‹‹(ሙሐመድሆይ!) ለዓለማትም እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።›› (አል አንቢያእ 107)157

2. ለመውሊድ ማረድን አስመልክቶ፦

عَنْ أَنَسٍ رَضِيَ اللَّهُ عَنْهُ: (أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ عَقَّ عَنْ نَفْسِهِ بَعْدَ النُّبُوَّةِ). [رواه البيهقي]
ሰይዲና አነስ (ረ.ዐ) እንዳስተላለፉት፦ "የአላህ መልክተኛ ነብይ ከሆኑ በኋላ ለራሳቸው አቂቃ አውጥተዋል።" (በይሀቂ ዘግበውታል)

ኢማሙ አስ-ሱዩጢ እንዲህ ይላሉ፦ "ነብዩ በሰባተኛ ቀን አያታቸው አቂቃ እንዳወጡላቸው የታወቀ ነው። በኢስላም ደግሞ ሁለት አቂቃ የለም፤ ስለዚህ እርሳቸው ያወጡት አላህን ለማመስገን ነው።"ሁስኑል መቅሰድ ፊ ዓመሊል መውሊድ

ነብዩ (ﷺ) ለውልደታቸው የነበራቸው ትኩረት

ነብዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ስለ ሰኞ ቀን ጾም በተጠየቁ ጊዜ እንዲህ ብለዋል፦

فِيهِ وُلِدْتُ وَفِيهِ أُنْزِلَ عَلَيَّ. [رواه مسلم]
ትርጉም፦ "እርሱ እኔ የተወለድኩበትና (ቁርኣን) በእኔ ላይ መውረድ የጀመረበት ቀን ነው።" አሉ
(ሙስሊም ዘግበውታል)

"አሚሩል ሙእሚኒን ፊል ሐዲስ" በመባል የሚታወቁትና የቡኻሪ ማብራሪያ (ፈትሁል ባሪ) አዘጋጅ የሆኑት ኢብኑ

ሐጀር አል-ዐስቀላኒ እንዲህ ይላሉ፦
‹‹አላህ ጸጋ በመለገስ ወይም ጉዳትን በማስወገድ ለዋለዉ ዉለታ እንደ ሱጁድ፣ጾም፣ሶደቃና ቁርአን መቅራት ባሉ ዒባዳዎች ምስጋና ማድረስና ይህ
ዉለታዉ የተፈጸመበትን ቀን እየጠበቁ በየዓመቱ ምስጋናዉን መደጋገም ተገቢ መሆኑን ከዚህ ሀዲስ እንማራለን። ይህ የእዝነት ነብይ ከመወለዳቸዉ የበለጠ ምን ጸጋ አለ?»
(አል ሃዊ ሊለፈታዊ)

ሰሐቦች ተሰባስበው አላህን ሲያመሰግኑ፦

أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ خَرَجَ عَلَى حَلْقَةٍ مِنْ أَصْحَابِهِ فَقَالَ: «مَا أَجْلَسَكُمْ؟» قَالُوا: جَلَسْنَا نَدْعُو اللَّهَ وَنَحْمَدُهُ عَلَى مَا هَدَانَا لِدِينِهِ وَمَنَّ عَلَيْنَا بِكَ. قَالَ: «آللَّهِ مَا أَجْلَسَكُمْ إِلَّا ذَلِكَ؟» قَالُوا: آللَّهِ مَا أَجْلَسَنَا إِلَّا ذَلِكَ. قَالَ: «أَمَا إِنِّي لَمْ أَسْتَحْلِفْكُمْ تُهْمَةً لَكُمْ وَإِنَّمَا أَتَانِي جِبْرِيلُ عَلَيْهِ السَّلَامُ فَأَخْبَرَنِي أَنَّ اللَّهَ عَزَّ وَجَلَّ يُبَاهِي بِكُمُ الْمَلَائِكَةَ». [رواه النسائي]

"የአላህ መልዕክተኛ ወደባልደረቦቻቸዉ አንድ
ስብስብ ወጡና፦‹‹የተቀመጣችሁት ለምን ጉዳይ ነዉ?›› ሲሉ ጠየቁ።
‹‹አላህን ለማስታወስ (ለዚክር) እና ወደእስልምና ስለመራን፣እንዲሁም ጸጋዉን ስለሰጠን ልናመሰግነዉ›› አሉ።‹‹በአላህ ማሉልኝ፤ ከዚህ ዉጭ ሌላ ያስቀመጣችሁ ጉዳይ የለምን?›› ሲሉ ጠየቋቸዉ። ‹‹ጉዳያችን ይህ ብቻ ነዉ›› ሲሉ መለሱ። ‹‹ ያስማልኳችሁ ቃላችሁን ተጠራጥሬ
አይደለም። ግና ጅብሪል ከኔ ዘንድ መጥቶ አላህ በመላኢኮች ላይ በናንተ እየተኩራራ እንደሆነ ነገረኝ›› አሉ።
(ነሳኢ ዘግበውታል)417

መንዙማ ፤ ዘንበል ዘንበል ማለትና የአንሷሮች ተግባር

መንዙማና ዘንበል ዘንበል ማለት ፦

أَنَّ الْحَبَشَةَ كَانُوا يَزْفِنُونَ بَيْنَ يَدَيْ رَسُولِ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ ـ وَيَتَكَلَّمُونَ بِكَلَامٍ لَا يَفْهَمُهُ فَقَالَ رَسُولُ اللَّهِ صَلَّى اللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمَ: «مَا يَقُولُونَ؟» قَالُوا: يَقُولُونَ: مُحَمَّدٌ عَبْدٌ صَالِحٌ. [رواه ابن ماجه]
"ሐበሻዎች በአላህ መልክተኛ (ﷺ) ፊት እርሳቸው የማያረዱትን ነገር እየተናገሩ ይጨፍሩ ነበር ። የአላህ መልክተኛም፦ «ምንድነው የሚሉት?» ሲሉ ጠየቁ። ሰሐቦቹም፦ "ሙሐመድ ደጉ ባሪያ እያሉ ነው" አሉ።
(ኢበኑ ማጃህ ዘግበውታል)

ሁሉንም ዓይነት ሥራዎች በአንድ ላይ

ወደ ታሪኩ ስንገባ ኢማሙ ሲዩጢ «አድ-ዱሩል መንሱር» ላይ እንዲሁም ኢብኑ ተይሚያ «ኢቅቲዳኡስ አስ-ሲራጢል ሙስጠቂም» በሚባለው ኪታባቸው ላይ ዐብድ ኢብኑ ሑመይድንና ኢብኑ ሲሪንን በመጥቀስ ሰሂህ በሆነ ሰነድ ዘግበውታል።

አንሷሮች (የመዲና ነዋሪዎች) የአላህ መልክተኛ (ﷺ) ወደ መዲና ከመምጣታቸው በፊት እንዲህ አሉ፦ "አንድ ቀን ተሰባስበን አላህ ስለዋለልን ታላቅ ውለታ ብንተዋወስና ብናመሰግንስ?"

"ቅዳሜ ቀን ይሁን" አሉ፤ ከዚያም "ቅዳሜ አይሁዳውያንን መምሰል/መግጠም ይሆናል" ብለው ተዉት።

"እሁድ ይሁን" አሉ፤ ከዚያም "እሁድ ነሳራዎችን መምሰል ይሆናል" ብለው ተዉት።

"የዐሩባ ቀን ይሁን" አሉ (በጃሒልያ ዘመን ጁሙዓን ዐሩባ ይሉት ነበር)። በዚህ ተስማምተው በአቡ ኡማማህ ሰዕድ ኢብኑ ዙራራህ ቤት ተሰባሰቡ በግ ታረደላቸው ተመገቡ ።

እስኪ ልብ በሉ! ከላይ ከተጠቀሱት የመውሊድ ተግባራት ውጪ ምን ይደረጋል?

1. አንድ ቀን እንምረጥ አሉ (ቀን መረጡ)
2. ተሰባሰቡ (ጀማዓ ሆኑ)
3. እንስሳ አረዱ (ምግብ አዘጋጁ)
4. ስለተዋለው ጸጋ እንተዋወስ አሉ።

ለመሆኑ መውሊድ ከዚህ ውጪ ሌላ ምን አዲስ ነገር አለው? አንሷሮች (ረ.ዐ) የሠሩትን በጎ ሥራ አይደለምን የምንደግመው? ወላሂ ከአንሷሮች ሥራ የስንዝር ያህል እንኳ አላፈነገጥንም!

ወቢላሂ ተውፊቅ